# ሌላው ባርነት !!

በታምራት የማነ (besrattam@gmail.com ) 04-15-18

በአሁኑ ጊዜ በመላው ሃገራችን በተለያዩ አቅጣጫዎች በቂም ባይሆን የስራ እድል ተፈጥሯል ፡፡የስራ እድል መፈጠሩ ጥሩ ቢሆንም አንዳንድ ሳናካዎች መታየት ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥሯል ፡፡ይህም በኢፌድሪ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ያልሰፈረ ራሱን የቻለ አዋጅ መመሪያ ያልወጣለት የቅጥር ዓይነት ስላለ ነው -ሌላው ባርነት ያሰኘኝ ፡፡ከሶስትና አራት ዓመት በፊት አዲስ አበባ በአንዳንድ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በኤጀንሲ በሚቀጠሩ ሰራተኞች የሚታዩኝ ኢሰብአዊ የቅጥር ሁኔታ ተዘዋውሬ በማየት በተቻለኝ ዓቅም ይህንን በተመለከተ ለማጣራት ሞክሬ ነበር የዓቅም ጉዳይ ሆኖብኝ እንዳቆመው ተገድጃለሁ ፡፡

ጉዳዩ ስለ ቅጥር ሰራተኞች በአሰሪ ኤጀንሲዎች የሚደርስባቸው በደልና ግፍ ነው ፡፡ በአሁኑ ጊዜ በተለይ በዚህ 10 ዓመትውስጥ በመላው ሃገራችን በአዲስ አበባም ይሁን በተለያዩ የክልል ከተሞች አንዳንድ ፋብሪካዎችና የመንግስት መ/ቤቶች የቅጥር ደንብ በሲቪል ሰርቪስ የሰራተኞች የስራ መደብ የጥጉና ፅዧ መደቦች ( ጥበቃና ጉልበት ) (ፅህፈት ና ፅዳት ከራሱ ቅጥር አውጥቶ በኮንትራት መልክ ለውጭ ቀጣሪዎች በመስጠት (Out Source ) ስራ ለማቀላጠፍ በሚል ኢትዮጵያዊ የሆኑ አስቀጣሪዎች አሉ ፡፡ቀጣሪዎቹ ከድርጅቱ ባለቤት ሙሉውን ገንዘብ ይወስዱና እነሱ ስራውን ይሰሩታል ፡፡ተቀጣሪው ግኑኝነቱ ከዋናው ሳይሆን ከሶስተኛ ወገን ነው፡፡

እነኝህ አስቀጣሪዎች በአጠቃላይ የቅጥራቸው አይነትና ለሰራተኛው የሚሰጡት ክፍያና አገልግሎት ሰብአዊ ህግ የሚጥስ ነው ፡፡ኤጀንሲዎቹ አንዳንድ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የጥበቃና ጉልበት እንዲሁም የፅዳትና አሁንማ ሌሎች የቢሮ ስራዎች ሁሉ ባካተተ መልኩ ወደ ውጭ በማውጣት ኮንትራት ይወስዳሉ ፡፡ ለነገሩማ ስራ ለማሳላጥ ነው ተብሎ የሚጠራው ግና ድብቁ ብዝበዛ እና ሌላው ባርነት ነው ፡፡ አሁን አሁንማ ሌላው ሃብት ማካበቻ ዘዴ ሆኗል ፡፡እዚህ ላይ አንባቢ ሊረዳልኝ የሚገባው ከየመሰሪያ ቤቱ እና ድርጅቶቹ ስራውን ለኛ ስጡን እኛ እንሰራላችኋለን ብለው ነው እንጂ ጨረታ የሚባል የለም በስምምነት ኮንትራት ይወስዳሉ ፡፡ በዚህ ወቅተ ኤጀንሲዎቹ ስራውን (ቀጥሮ ለማስተዳደርና ለመስራት ) ከዋናው ከድርጅቱ የሚወስደው እስከ በርከት ያለ እንደሆነ ነው ወሬውን የሰማሁትና ከተቀጣሪዎቹ ያገኘሁት መረጃ ፡፡አሰሪው ከድርጅቱ የሚወስደው ብር በሺዎች የሚቆጠር ሲሆን ኤጀንሲዎቹ ግና ለሰራተኛው ግና በወር እስከ ስድስተ መቶ ብር ሊያውም የስራ ግብር ተቆርጦባት ይሠጠዋል -አንድ በሉ ፡፡

የተቀጣሪው በአጀንሲው የስራ ሰዓት ከንጋት 12፡00 ሰዓት ገብቶ ማታ 12 ሰዓት ይወጣል ፡፡ ከስምንት ሰዓት በላይ ያለ ምሳ ሰዓት እንዲሰሩ ይደረጋል ፡፡ በዓመት ሁለቴ ደንብ ልብስ ይሰጠዋል ፤ዕድል ሆኖ አዲስ ቅጥር ከሆንክ እስኪሰፋልህ የተሰናበተ ሰራተኛ ሲለብሰው የነበረ ልብስ እንድትለብስ ይደረጋል ፡፡የጤና ወጪ ሽፋን የለም ፤እረፍት የለም ከእሁድ እስከ እሁድ ስራ ነው ፡፡ባጋጣሚ ሃዘን ህመም ወይ ሌላ ተያያዥ ችግሮች ገጥሞት/ሟት ሰራተኛው/ዋ ከስራ ብት/ቢቀር ከማስጠንቀቂያ ጋር ደመወዟ/ዙ ይቆረጣል ፡፡እኒዘህ ኤጀንሲዎች ሰራተኛው የሚፈፅሙት ሌላው ላይ አስነዋሪ ተግባር ክፍያ እንዲጨምርለት ፍላጎት ካለው ሌላ ተጨማሪ የስራ ግዴታ ውል እንዲፈርም ይደረጋል ፡፡ በዚህም ሰራተኛው/ዋ ለተጨማሪ ክፍያ ተጨማሪ ስራ በሚሰሩበት ወቅት ለምሳሌ አንድ ባንክ ወይ ሌላ ድርጅት የተቀጠረ ንጋት 12 ሰዓት ማታ ሲወጣ በዚያው ቅፅበት ወዲያውኑ ወደ ሌላ ድርጅት ይወስደውና ከዚያች ሰዓት ጀምሮ እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት ይሰራል ጥበቃውን ግዳጁን ይፈፅማል ፡፡ልብ በሉ ሃያ አራት ሰዓት ይሰራል ያለ እረፍት ፤የሃገራችን የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ህግ "አንድ ሰው በቀንስምንት ሰዓት መንግስት የደነገገው የአረፍት ቀንም ....." የሚለው አዋጅ እነዚህን ድርጅቶችን አይመለከትም ፡፡እኔ በወር ሰላሳ ቀናት ውስጥ ሃያ ቀን ነው የምሰራው እነኝህ ዜጎች ግና በአሰሪ በኤጀንሲዎች

ግፈኛ አሰራር ይህ/ች ሰራተኛ ሰላሳ ቀናት በወር ስትሰራ ሌትና ቀን ጨምሮ ስድሳ ቀናት ይሰራል/ትሰራለች ማለት ነው ፡፡

ይህ ስራን ለሌላ ኤጀንሲ አካል አሳልፎ መስጠት ስራ ለማሳለጥ ሲባል ነው የሚል ወሬዎችን እሰማለሁ ፡፡ግና አሁን አሁን ብዙዎቹ ወደዚህ ስራዎችን ለኤጀንሲ አሳልፎ መስጠት እንደ ኪራይ መሰብሰቢያም ሳይውል እናዳልቀረ ከነጭራሹ ዜጎች እንደ ባርያ በማሰራት ዜጎችን በሌላ ባርነት መግዛት ሆኗል ፡፡ ግለሰቦች በድሃውና ከገጠር ስራ ፍለጋ የሚፈልሰው በተለይ ሴት እህቶቻችን ዓላማ ያደረገ ነው ፡፡ አንዳንድ በራሳቸው ቀጥረው ሲያሰሩና ለኤጀንሲው ሰጥተው ስራው ሲሰራ በተለያየ ሁኔታ ውጤታማና አርኪ ስራ እንደማይሰራ ነው የሚሰማውና የሚታየው ቡዙ ልዩነቶች አሉት ፡፡ይህም ተቀጣሪዎቹ ቀጣሪያቸው ከዋናው በብዙ ብር ወስዶ ለሰራተኛው የሚሰጠው መጠን በጣም አነስተኛ እንዳይኖር እንዳይሞት የሚያርግ ነው ፡፡ በአሁኑ ጊዜ አንድ ሰው ቤተሰብ ያለው አባወራ ወይ አማወራ 650 ብር እንዴት ነው ፍትሃዊ ክፍያ የሚሆነው ፡፡ሊያውም ሙሉ ቀን በር ላይ ቆማ/ሞጎንበስ ቀና እያለ ጥበቃ ስራና የፅዳት ስራ ፡፡ከሰኞ እሰከ እሁድ ዕረፍት የለ ህክምና የለ የአለቃ ማንጓጠጥ ተጨምሮብት !!

በዚህ ኤጀንሲዎች ሰራተኛው ላይ የሚፈፅሙት ሌላው ግፍ ይህ ሰራተኛ ዋስ ለማቅረብ ካልቻለ ብር ያስይዛል እሰከ ሁለት ሺ አምስት መቶ ብር ያስይዛል ፡፡ እዚህ ድርጅት ማንም ሰው ማጣራት የሚችለው ግፉ በዝቶበት የሚወጣ እንጂ በድርጅቱ ትእዛዝ የሚሰናበት ሰራተኛ የለም ፡፡ ይህ ሰራተኛ ልልቀቅ ቢል አይፈቀድለትም፡፡እዚህ ሰራ ላይ የሚሰማሩት አብዛኞቹ አይታቸሁ ከሆነ ከክልል የሚመጡ ሰራ ያጡ የአርሶ አደር ልጆቸ ናቸው ፡፡ባንድ ወቅት አንድ የክልል ወጣት ዋስ ስሌለው ብር ነበር ያስያዘውና ባጋጣሚ እናቴ ታማለች እና ገጠር ሄጄ ማስታመም እፈልጋለሁ ብሎ ሲጠይቅ "ውሸትህ ነው ....." ብለው ሞገቱት ፡፡ሰራተኛው የወላጅ ነገር ነውና ጥሎ ሄደ ወላጅ እናቱን አሳክሞ ሲመለስ ብሩንም አልሰጡትም ማን ሊያናግረው ልጁን ባጋጣሚ አግኝቸው ማስረጃውን ሰጥቶኛል ፡፡ይህ ምን ይሉታል ? ሌላው አስገራሚ ነገር ሰራተኛ ካጠፋ ቅጣቱ እንደ ወታደራዊ ቅጣት ነው (ቁጭ በል ብድግ አኮብኩብ ) -አሰገራሚስነ ምግባር የጎደላቸው የኤጀንሲ ተቀጣሪዎች ፡፡መንግስት እንዴት ዜጎቹ ላይ ይህ እንዲሆን ይፈቅዳል ??

የሚታይ የቅጥር ዓይነት አስገራሚ ነው ፡፡ሲጀመር ከአስር ዓመት በፊት ትረስት በሚል የአሰሪ ድርጅት ነበር የተጀመረው ፡፡በአሁኑ ጊዜ ግን ስማቸውና ተግባራቸው ኢትዮጵያውነት ያልተላባሰ ስነ ምግባርና የቅጥር ዓይነታቸውሀገራችን ከፈረመቻቸው ዓለም ዓቀፍ ህግጋትና ድንጋጌዎች ያፈነገጡ ናቸው ፡፡ምናልባት ሌላ ሃገርም አለ'ኮ የምትሉኝ የዋሃን አትታጡም ይሁን ከኢትዮጵያ ውጭ ያላችሁታውቃላችሁ ክብርህ ተጠብቆ እረፍት አለው የጤና ሽፋን ያለው ህግና ደንብን የተከተለ ነው ፡፡ እዚህ ያለው ጭራሽ ኢሰብአዊ ስራ እየተሰራ ነው ፡፡

እዚህ ላይ ልትረዱልኝ የሚገባው ይህን በተመለከተ በአዲስ አበባ እስጢፋኖስ አካባቢ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሰራተኞች ፌደሬሽን ፅ/ቤት ጉዳዩ በተመለከተ ሄጄ ሳነጋግራቸው " እነኝህ ኤጀንሲዎች በኢትዮጵያ የሰራተኛ ማህበራት አልተመዘገቡም እና ለጊዜው በዚህ ጉዳይ ከመንግሰት ጋራ እየተወያየነበት ነው " ብለውኛል ፡፡ የእነኙህ አሰሪዎች ኤጀንሲ የስራ ፈቃዳቸው ራሱ በምን መልኩና በየትኛው ህግ እንደተሰጣቸው በውል ሊያስረዳህ የሚችል አካል የለም - ብዙ ቦታ ብንከራተትም የሚመለከተው አካል ሊነግርህ የሚችል የለም ፡፡ንግድ ቢሮ ሰትሄድ እኔ ፈቃድ ስጠኝ አለኝ ሰጠሁ ...ሁሉም በየፊናው ሰርቻለሁ ነው ሚለው እንጂ ሃላፊነት ወስዶ ምለሽ የሚሰጥ አካል የለም ፡፡ ኤጀንሲዎች የንፁህ ኢትዮጵያዊ ወንድማቸውና እህታቸው ላብና ጉልበት እየበዘበዙ ማየት ያማል፡፡አሁን አሁንማባቋራጭዋናው ምንጭ በመሆኑ የሆነ ግለሰብ ከመሬት ተነስቶ ኤጀንሲ ያቋቁም ጀመረ ፡፡አንጋፋ ድርጅቶችንና የመንግስት ተቋማት የተወሰኑ የስራ ፕሮግራማቸውን ለኤጀንሲ በመስጠት ለብዝበዛው የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እያደረጉ ነው ፡፡ ስራው አሁን አሁን አሪፍ ቢዝነስ ህገወጥ ስራን ህግን ሽፋን አድርጎ የሰው ጉልበት በመበዝበዝ ትርፍ ማጋበስ ጥሩ ስራ ሆኗል ፡፡የሞያ ብቃት አይጠይቅ ፍቃድ ሲሰጥ ኮንትራት ውሉ ለሰራተኛው እንጂ ለአስቀጣሪዎቹ ምቹ የሆነ ስራ ነው ፡፡ፍቃዱን የሚሰጥ የመንግስት አካልም የሆነ ጊዜ ፍቃዱን

ሰጥቷቸው ሲያበቃ  ለምን ኣላማ ፍቃዱን እንደወሰዱት ክትትል ኣያደርግም -ለምን ሲባል ሰዎቹ ኣሁን ኣሁን እንጂ ድሮማ (ከስድስት ዓመት ) ኣይነኬዎቹ ነበሩ -ይባላል ፡፡

የኤጀንሲዎች ንብረት ሰራተኛው ለካልሲ ባጀት የለው ጫማው ተቦዳድሶ እነሱ ግና መኪኖቻቸው የቢሮ ስታይላቸው ለየት ያለ ነው ፡፡ለነገሩማ በዚህ ስራ ዘርፍ ያሉት በሃገራችን በተለያየ ሞያ ኣንቱታ ያተረፉ ሰዎች ናቸው ይባላል ፡፡ስለዚህ -ምን ማለት ይቻላል ፡፡

ስለዚህ ህግና ስርዓት ኣለን የአሰሪና ሰራተኛ ኣዋጅ ህግ ተደንግጎ ሳለ በህጉ ሳይሰራ ወጣት ስራ ማጣቱ ሳያንሰው ግለሰቦች ኪስ ማድለቢያ ሲሆን መንግስት የለም እንዴ ያስብላል ፡፡

በዚሁ ኣጋጣሚ መንግስት ርካሽ የሰው ሃይል እያለ ለውጭ ድርጅቶቸ ለኢንቨስትመንት ሲጋብዝ ብዙ ችግሮች እያጋጠሙ ነው ፡፡ከሁለት ዓመት በፊት ፌደራል መንግስት ኮሚዩኒኬሽን ባዘጋጀው ጉብኝት ወደ አቃቂ ቢሾፍቱ ኣዳማ ትላልቅ የውጭ ኢንቨስትመንቶች  ውስጥ ያየሁት የዚህ ነፀብራቅ ነው ፡፡ይህ የውጭ ኢንቨሰተሮችንና ኤጀንሲዎች ጋር ያለው ችግር  ለሰራተኛው የሚሰጡት ክፍያ እጅግ ቀደም ሲል እንደገለፀኩት ነው  ..ደመወዙና የሰራተኛው ኣያያዝ ብዙ የሚባልበት ስለሆነ መንግስት የሃገሪቱ የሁሉም ምንጭ የሆኑትን ሴት እህቶቻችን በተመለከተ ምን እየሰራ ነው ፡፡

ወጣቷ ዓረብ ሃገር ሄዳ ከፎቅ ተወረወረች ፡ ያለ ገደብ ትሰራለች ---ብዙ እየተባለ በተለያዩ የዓለም ኣቀፍና ሃገር ውስጥ ሚድያዎች ብዙ ይነገራል ፡፡ ወገኑ በራሱ ወገን ሌላ ባርነት ውስጥ እያስገባ ያለው  መንግስትና ህግ ባለበት ሃገር ነውን? ስለዚህ መንግስት እንዴት በገዛ ሃገሩ ዜጎች ላይ በኢንቨሰትመንት ስምና የኢጀንሲ ቀጣሪዎች ኣፀያፊ ስራና ተግባር ወጣቱ እየተበዘበዘ ፤ለምን ዝም ኣለ ?ለምንስ ሚድያዎቹ ዝምታን መረጡ ...? ዋናው ባለጉዳይ መንግስትስ ስለ ዓረብ ሀገሮች የሚገኙ ዜጎቹ ሲጨነቅና ሲጠበብ ምነው ስለ ሃገር ውስጥ  ሌላው ባርነት ምነው ልሳኑ ተዘጋ ??